# <u>ትብብር ከማን ጋር? ዓላማውና ልዕለ-ግቡስ?</u>
## ኢትዮጵያን ለማዳንና ሕዝቧን ለመታደግ ኢትዮጵያዊ አስተሣሰብንና እምነትን ይጠይቃል!

*(ክፍል ሦስት - ካለፈው የቀጠለ)*
*ከአያልሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት (ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፪ ሀሽ ፫ ዓ/ም)*

ይሁንናም የዚኽ ድርጅት መሪዎች ሲወጓትና ጥፋቷን በሚመኙላት ኢትዮጵያ በምትባል አገር ሥር "የክልል-መንግሥት" መሥርቶ አካባቢውን "በማስተዳደር" መወሰን የነሱ ግብ ስላልሆነ፣ ያገኙትን አዲስ "አጋጣሚ" በመጠቀም "በሕዝበ-ውሳኔ" ስም የመገንጠል ዓላማቸውን ለማሣካት ተጣደፉ:: ያ መሠሪያዊ እርምጃም ለአዲሶቹ የኢሕአዴግ መሪዎች የተያያዙት በታሪክም ሆነ በምንም ተደጋፊነትና ተቀባይነት የሌለው የጎሣ "ፌደሬሽን" የሚያስከትለውን ማጣፊያው-ያጠረ አደጋ በመጠኑ እንዲገነዘቡ ያደረገና ለወደ-ፊትም ያ ከፋፋይ መርኃ-እቅዳቸው (ፖሊሲያቸው) ሊያስከትል ስለሚችለው አደጋ የማስገንዘቢያ-ደወል የደወለ ክስተት ነበር ማለት ይቻላል:: ኢሕአዴግ ያንን ፍላጎታቸውን ማሟላት ስላልቻለም ይኽ ኃይል አኩርፎ ተመልሶ ጫካ እንዲገባ እንዳደረገው ይታወቃል:: የ"ኦብነግ" አነሣስም ሆነ እምነት፣ የለየለት ፀረ-ኢትዮጵያ እንደሆነና ዓላማውም አንድ-አምሥተኛ የሆነውን የአገሪቱን ክፍል ለመገንጠል፣ ችግሩም ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር መሆኑን በፕሮግራሙ ላይ ብቻ ሣይሆን በተግባር ያረጋገጠ ቡድን ነው:: (ስለዚኽ ድርጅት ታሪክና ዓላማው "Quo Vadis Ethiopia? (Ethiopia Wodet?" በሚል ርዕስ በተከታታይ በወጣው ጽሑፍ ላይ በተለይ በክፍል ሦስት በመጠኑ ለማሣየት ሞክሬአለሁ::)

በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የሞት ፍርድ የፈረደው የለንደን ጉባዔ ተሣታፊና አሥራ-ሁለት መቀመጫዎችን ይዞ የ"ሽግግር መንግሥት" አናሣ ሽሪክ የነበረው "የኦሮሞ ነፃ-አውጭ ድርጅት" (ኦነግ) ከ"ሽግግር መንግሥቱ" አውራ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር ብዙ ሣይውል ሣያድር ቅራኔ ውስጥ መግባቱ ይታወቃል:: የኦነግ መሪዎች በመስክ ላይ ያለውን ሃቅ እና የኃይል ሚዛን እንዲሁም የሕወሓት መሪዎች ከማንም ጋር በአቻና በእኩልነት አብሮ ለመሥራት ምንም ዓይነት ሥነ-ልቦናዊ ዝግጁነት እንደሌላቸውና ሁሉም በነሱ ሥር እነሱ የሚሉትን አሜን ብሎና መጥነው የሰጡትን ተቀብሎ በተከታይነት እንዲያጅባቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን በጊዜው የተረዱ አይመስሉም:: በራሣቸው የተናጠል ብይን ብቻ ለራሣቸው ሥልጣን ማደላደያ ያገለግሏቸው ዘንድ አስልተው የወሰዷቸውን አንዳንድ ታሪካዊ ድጋፍና ተቀባይነት የሌላቸው እርምጃዎች በማስረጃነት በማቅረብ ለኦነግ፣ አልፎም ለሠፊው የኦሮሞ ሕዝብ፣ ታላቅ ውለታዎችን እንደ-ዋሉ በቆጠሩት የሕወሓት መሪዎችና ከዚያ በላይ በጠበቁና 'ታናሽ ሽሪክ' ሆኖ መታየትን ለመቀበል ያልተዘጋጁት የኦነግ መሪዎች መኻል ልዩነት መከሰቱ አይቀሬ ነበር:: ኦነግ በጋራ ካቋቋመው "ሽግግር መንግሥት" ሲለይና አፍሮ (አኩርፎ) ተመልሶ ጫካ ለመግባት ሲወስን ያነሣው ጥያቄ ኢሕአዴግ "የሰጠኝ" አልበቃኝም ከሚል የተነሣ እንጂ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠየቀውና በቀጣይነት ከሚታገልበት የዴሞክራሲ እሴቶች እውን መሆን ጋር የተያያዘ እንዳልሆነም የዚያኑ ያኽል ግልጥ ነው::

ቀደም-ሲል በጥር ወር ሰማንያ-ሦስት ዓ/ም በሽዓብያና በኦነግ ጣምራ ዘማች ኃይል በአሦሳ ከሦስት-መቶ በላይ የሚሆኑ ንፁኃን ዜጎች "አማሮች" ተብለው በግፍ እንደ-ተጨፈጨፉ በወቅቱ መዘገቡ ይታወቃል:: በተመሣሣይ ሁኔታ በኢሕአዴግ "የሽግግር መንግሥት" ጊዜ በአርባ-ጉጉና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች በተለይም "አማራ" ወይም "ክርስቲያን" ናቸው በተባሉ ዜጎች ላይ በተፈጸመው አሰቃቂ ግድያና የዘር-ምንጠራ የግፍ እርምጃዎች የብዙ ንፀኃን ዜጎች ሕይዎት እንደ-ጠፋና ሥፍር-ቁጥር የሌላቸው ደግሞ ከተወለዱበትና ካደጉበት መፈናቀልና ንብረታቸውን መነጠቅ፣ ወዘተ.. በተመለከተ በቀጥታ ተጠያቂ ከሆኑት ቡድኖች ውስጥ ኦነግና "በሽግግር" መንግሥቱ ውስጥ ሦስት መቀመፃዎች የነበሩት "የኦሮሞ ነፃ-አውጭ እስላማዊ ግንባር - (IFLO)" የተባለው ቡድን በቀዳሚነት የሚጠቀሱ እንደሆነ የታወቀ ነው:: በወቅቱ 'የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት መረብ በሆላንድ (ETHIOPIAN INFORMATION SERVICE NETWORK IN HOLLAND - SHINE)' የተሰኘው ድርጅት በቀጥታ ከቦታው የተገኘውን መረጃና ለሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔና ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ የተላከውን ደብዳቤ ወደ-እንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሞ ባወጣው ሰነድ ላይ እንደተዘገበው፤ በአርባ-ጉጉ ለደረሰው ጭፍጨፋ የተገደሉትን ሰዎች ስም፣ ቦታና ቀን፣ ሁኔታና ለዚኽም ዘር-ማጥፋት ዘመቻ አስተባባሪና መሪ የነበሩትን ቢያንስ ሰባት የኦነግ የጦር መሪዎች ስም ዝርዝር ጭምር ይፋ ሆኗል:: (*)

እንደሚታወቀው በዚኽ ጉዳይ ላይ በነዚኽ ወንጀለኞች ላይም ይሁን በድርጅቱ ኦነግ ላይ

(*) *የወንጀሉ ግንባር-ቀደም አስተባባሪና መሪ ተብለው ከተጠቀሱት መኻል ሱልጣን ከድር፣ ረሻድ ፌቶ፣ አሕመድ አማን፣ ቱቱና ከድር፣ ጅብሪል ሸኽ ሙክታር፣ ጌይላና ሐጊሁም፣ ሲኩዋሬ ሣኔ ይገኙበታል::*

በአዲሶቹ ገዥዎች የተወሰደ አንዳችም ሕጋዊ እርምጃ አልነበረም። ድርጅቱም ለዚኽ የሰው-ዘር ማጥፋት ኢ-ሰብዓዊ ወንጀል፣ እኔ እስከማውቅ ድረስ፣ አንዳችም ኃላፊነት አልወሰደም። አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵውያንም ቢሆኑ ሥራየ ብለው ቀጣይነት ያለውና ውጤት ያስመዘገበ ክትትል ስላላደረጉ፣ ታላቁ ሰላማዊ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪና የእኩልነት ታጋይ ክቡር ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ "ለአንድ ሰው የተነፈገ ፍትኅ ለሁሉም እንደተነፈገ ይቆጠራል" እንዳሉት ሁሉ የዚያ አሰቃቂ የግፍ ሰለባ የሆኑ ወገኖች ብቻ ሣይሆኑ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፍትኅ እንደተነፈጋቸው ልብ ሊባል ይገባል።

ያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ዴሞክራት ኃይሎች በተለይ ኦነግን እንደ-ጠላት ያዩበት ጊዜ አልነበረም። ምንም እንኳን ይኽ ቡድን ኢትዮጵያውያን በሚያደርጉት የፍትኅና የእኩልነት ትግል የጋራ የእንቅስቃሴው አካል እንዲሆን በተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ አራሱን እንደ-ሦስተኛ ኃይል የመቁጠር ባኅሪ በተደጋጋሚ ያሣየ ቢሆንም፣ ተቃዋሚው ክፍል ባደረጋቸው በመርኅ ደረጃ አግላይነት የሌላቸው የመሰባሰብ ሙከራዎች ሁሉ ተሣታፊ እንዲሆን ያልተጋበዘበት ጊዜ አልነበረም። በተለይ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በኩል በከፍተኛ ትዕግሥት ድርጅቱ ምናልባት ወደ-መኻል ሊመጣ ቢችል ዕድል ይሰጠው ከሚል አስተሣሰብ ከመንገድ በወጣ መልክ ሣይቀር ጥረት ተደርጓል። አልፎም ድኅረ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት የተከሰተው የፖለቲካ ምስቅልቅል መፍታት እንዲቻል በምርጫው በቀጥታ የተሣተፉ ብቻ ሣይሆን አግላይነት የሌለው ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት ብሎ ባቀረበው አሣብ ላይ ሣይቀር ኦነግም እንዲጨመር መጠየቁ ይታወቃል። ምንም እንኳን በዚኽ ቡድን ውስጥ እንደ-አባ ብያ ዓይነት ጨዋ፣ ተግባቢና የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ የቋንቋ ክፍሎች ጋር ተባብሮ በሚደረግ የጋራ ትግል መልስ ማስገኘት ይቻላል ብለው የሚያምኑ አንድ-ሁለት ተብለው የሚቆጠሩ ግለሰቦች ሊኖሩ ቢችሉም፣ ድርጅቱ በድርጅት ደረጃ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ትርጉም ያለው ሥራ ለመሥራት የቻለበት ጊዜ የለም። እስከ-አሁን ድረስ እንደ ፓሪስ-አንድ የመሣሰሉ አንዳድ የድርጅቶች ስብሰባዎች ላይ አልፎ አልፎ ከመሣተፍ ውጭ ኦነግ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ እሴቶች እውን እንዲሆኑና ሰብዓዊ መብት እንዲከበር በተደረጉ የጋራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሣታፊ የመሆን ፍላጎት አሣይቶ አያውቅም። ሌላው ቀርቶ ጠቅላላ የቅንጅት መሪዎችን ጨምሮ በብዙ አሥርተ-ሽህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለግፍ እስር ሲዳረጉና ሲንገላቱ፣ የታሰሩት እንዲፈቱ፣ በሕዝባችንም ላይ የሚደርሰው እንግልት፣ ግፍና ሰቆቃ ኅብረቱ የጋራ "የቀውጢ-ጊዜ ግብረ-ኃይል" እንዲቋቋም ባደረገው ጥረትም ይሁን በሌሎች ተመሣሣይ ጥረቶች ጉዳያችን ብለው ተሣታፊ መሆን አልፈለጉም። ያም የሆነበት ምክንያት ሌላ ሣይሆን እራሱን ከኢትዮጵያ ድርጅቶች ነጠል አድርጎ ስለሚያይና በተለይም ***"ከአብሲኒያ ቅኝ ግዛት ነፃ ለማድረግ"*** ነው የምታገለው ብሎ በገሃድ የያዘው እምነትና የቆመበት ዓላማ ስለ-ማያስችለው ብቻ ነው።

አንዳንድ ወገኖች በነዚኽ ቡድኖች ላይም ሆነ በአጠቃላይ በፖለቲካዊ ኀጠኝነት/ ኀሠኝነት ላይ የሚሰጥን ትችትም ሆነ ተቃውሞ ትክክል አለ-መሆኑን ለማሣመን "እነኝኽ ክስተቶች 'በመስክ ላይ ያሉ እውነታዎች ወይም ሃቆች' (realities) ስለሆኑ 'ተቀብሎ' ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የለም" የሚል ክርክር ያነሣሉ። ይኽ እንግዲኽ ቡድኖቹን እነሱ "ቆመንለታል" የሚሉት ሕዝብ "ተወካይ" አድርጎ ከሚቀርበውና እነሱንም መተቸት ሕዝቡን "ቅር" እንደሚያሰኝ በተሣሣተ መልክ ከሚሰነዘረው የተዛባ አስተያየት ተጨማሪ መሆኑ ነው። እነኝኽ ወገኖች ከዚያ መከራከሪያ ነጥባቸው ጋር ያላዩት ሌላ ሃቅ ግን አለ። በመጀመሪያ ይኽንን አካሄድ የምንቃወም ወገኖች ቡድኖቹ የቆሙበትን ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም፣ የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአደረጃጀት ዘይቤ እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያቶች (አብዛኞቹ በየተወለዱበት አካባቢ ፀጥታ በማስከበር ስምም ይሁን በሌላ መንግሥት የሚወስዳቸው የግፍ እርምጃዎች በሚያስከትሉት የሁኔታዎች አስገዳጅነት) በየቡድኖቹ አባል ሆነው በሚገኙ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን (በግለሰቦቹ) ላይ የተነጣጠረ አይደለም። ሊሆንም አይችልም። እንደዚያ ዓይነት የጠላትነት አስተሣሰብ በዚያ ዓይነት አደረጃጀት ዘይቤ ከተሠለፉ ክፍሎች ቢመጣ ግን አይገርምም።

ሁለተኛ ግልጥ መሆን ያለበት ነገር የሚደረገው ትግል ለሥርዓት ለውጥ እንደ-ሆነ ነው። የሥርዓት ለውጥ ሲባል ደግሞ አንድ በሕዝብ ላይ የተጫነ ወይም የሰፈነ የመስክ ላይ "እውነታ/ ሃቅ" ሆኖ የሚገኝ ሥርዓትን በአዲስ የተሻለ ሥርዓት ለመተካት ነው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን "በመስክ ላይ ያለው እውነታ" ተራ ክስተት ሣይሆን ከዴሞክራሲ ጋር ትውውቅ በሌለው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የሚመራው ከፋፋይና ወደ-ኋላ ያየ ፖለቲካዊ የኀሠኝነት ሥርዓት ነው። የተጠቀሱት "በመስክ ላይ እውነታ" የሆኑ ድርጅቶችም ሆኑ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ደግሞ የዚኹ "የመስክ ላይ እውነታ" የሆነው ሥርዓት አካሎችም አራማጆችም ናቸው። በደቡብ አፍሪቃ የአፓርታይድ ዘረኛ ፍልሥፍና፣ በልዩ ልዩ አገሮች ላይ የተጫኑ ግፈኛ የቅኝ-ግዛት ሥርዓቶች፣ በአሜሪካ የሚኖሩ አፍሪቃዊ ዝርያ ያላቸው ወገኖችን እንደ ሦስት-አምስተኛ ሰው የሚቆጥር የባርነት ሥሪት፣

የፊውዳል ሥርዓቶች፣ ወዘተ.. እንዲሁም እነዚሁኑ ሥርዓቶች የሚያራምዱ ድርጅቶችና ተቋሞች ሁሉ በአንድ ወቅት ወይም በሌላ በኅብረተሰብ ላይ የተጫኑ 'እውነታዎች/ሃቆች' እንደ-ነበሩ ሁሉ፤ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ፖለቲካ ኅሠኝነትም ይሁን በዚኹ ፍልሥፍና የተደራጁ ድርጅቶች መኖራቸው በመስክ ላይ ያሉ 'እውነታዎች/ሃቆች' ናቸው:: እንግዴኽ ክርክሩን በሚያነሱ ወገኖች አመለካከትና ስሌት ከሆነ የደቡብ-አፍሪቃ ሠፊ ሕዝብ ዘረኛውን የአፓርታይድ ሥርዓት፣ ሚሊዮን ጭቁኖችም የተጫኑባቸውን አዋራጅና በዝባዥ የቅኝ-ገዥ ሥርዓቶችን፣ ፊውዳሎችን፣ አምባ-ገነኖችን፣ ኢትዮጵያውያንም የጣሊያን ወራሪዎችን፣ ደርግንም፣ ወዘተ 'በመስክ ላይ ያሉ እውነታዎች/ሃቆች' በመሆናቸው አሜን ብለው መቀበል ነበረባቸው እንደ-ማለት ይሆናል::

ስለዚኽ አንድም የሕወሓት/ኢሕአዴግ ከፋፍይና ኋላ-ቀር ፖለቲካዊ ኅሠኛ ሥርዓት እንዲሁም በዚሁ ፍልሥፍና የሚመሩ ቡድኖች እምነትና አቋም "በመስክ ላይ ያሉ እውነታዎች" ስለሆኑ በፀጋ መቀበል፣ አለያም ሥርዓቱንና የሥርዓቱ መቆሚያ የሆነውን ፍልሥፍና ከሥሩ መንግሎ መጣል ነው ምርጫው::

የሆነ-ሆኖ እነኝኽ ኃይሎች የዚኽ "አዲስ ትብብር" አካል ለመሆን "ተዘጋጅተዋል" ሲባል ሊገርም ከቶ አይገባም:: ለምን አይሉ? ምክንያቱም የዚኽ ዓይነት አካሄድ ከማንም በላይ እነሱን ነውና የሚጠቅመው:: አልፎው የዚኽ ዓይነት አካሄድ የበላይ ጠባቂ የሆነውና እነሱንም ልጓም አስገብቶ የሚያሽከረክራቸው ሸዓብያ በሥልጣን ላይ እየተንገዳገደ ለመቆየት የሚከተለው ፖሊሲ አካል በመሆን የሦስተኛ ኃይል ጥቅም አስጠባቂነት ሚናም ይኖረዋል:: እነዚኽ ኃይሎች ይኽንን "አዲስ አቋም" ያዙ ተብሎ በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ መቅረቡ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያንን የሚገርማቸው አልፎም የሚያሣስባቸውና የሚያንገበግባቸው ያ ለእነሱ ያስገኛል የተባለው ጥቅም በጋራው የፍትኅና የእኩልነት ትግል፣ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ኪሣራ ስለሚመጣ ነው:: በግንቦት-ሰባት ይሁን ወይም በሌላ ድርጅትም ይሁን ስብስብ በግልጥ ፀረ-አንድነት ዓላማ አንግበው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከሚታገሉ ቡድኖች ጋር የሚደረግ ይኽ "እሣትን በጉያ" ሊባል የሚችል አዲስ ዙር "ትብብር" ለእነዚኽ ክፍሎች ምን ጥቅም ያስገኝላቸዋል? ለኢትዮጵያስ/ለአንድነት ኃይሉስ ጉዳቱ ምንድን-ነው? ሥጋቱስ መሠረት አለው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሣታቸው የግድ ነው:: የመጨረሻውን በመጠኑ ቀደም-ሲል ከቡድኖቹ ተፈጥሮ-ባኅሪ ጀምሮ በተጠቀሱት ነጥቦች ለማሣየት ተሞክሯል:: እነዚኽ ፀረ-አንድነት ኃይሎች ይኽንን "ትብብር" ለምን በጉጉት ሊያዩት እንደሚችሉ ደግሞ ግልጥ ነው:: እነዚኽ ቡድኖች በኢትዮጵያ ስም ከተደራጁ ዴሞክራት ኃይሎች ተነጥለው እስከ-አሁን በሄዱበት የተናጠል መንገድ ዓላማዎቻቸውን የተሻለ መግፋት የማያስችላቸው እንደሆነ ከማንም በላይ እነሱ ተገንዝበውታል:: ያ ግን ኢትዮጵያዊው የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይል በሚያስበው፣ በሚመኘው ወይም በሚፈልገው መልክ 'የጋራ ትግል በማድረግ ተግባብቶና ተከባብሮ የጋራ አገርን መታደግና ሕዝብን ፍትኅንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ማድረግ፣ የአገር አንድነትንም ማስከበር' የሚያስችል ሣይሆን፤ ለእነዚኽ ኃይሎች ያ በጭንቅላቱ የቆመ አሠላለፍ የቆሙበትን አጀንዳ ግብ-አስጨባጭ፣ ቢያንስ ግን አንድ እርምጃ ወደዚያው የሚያስጠጋቸው አካሄድና ዘዴ እንዲሆን ነው ስሊታቸው:: በአጭር አነጋገር የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሉን ለግባቸው መረማመጃና መጠቀሚያ ማድረግ ማለት ነው::፣

አንደኛ እነዚኽ ኃይሎች ከሕወሓት ሂደት ትምሕርት ወስደዋል:: ሕወሓት እንደ-ስሙና እምነቱ ከሆነ እንደ-ድርጅ እንኳን አገራዊ ሥልጣን በብቸኝነት ለመያዝ ተከዜን የሚሻገርበት አንዳችም የሞራልም ይሁን ቁሣዊ ብቃት ሊኖረው ባልቻለ:: (እግዜር ያሣያችሁ "የጋምቤላ ነፃ-አውጭ"፣ ወይም "የአገው ነፃ-አውጭ" ወይም "የአማራ ነፃ-አውጭ"፣ "የኦሮሞ ነፃ-አውጭ"፣ ወዘተ.. የሚባል ድርጅት ትግራይ ውስጥ ገብቶ እንደ-ፈለገው ሕዝቡን ሲያምስ፣ ሲያተራምስና ቀጥቅጨ ልግዛ ሲል?!)

የነመለስ ዜናዊ ሕወሓት በወቅቱ ከኢሕአፓ ተነጥለው የሄዱ ወገኖችን "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ - ኢሕዴን" በሚል መጠሪያ ማደራጀቱ ይታወቃል:: የሕወሓት ጮሌዎች ግን እነዚያ ጭቆናን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለማንሣትና እኩልነትንና ፍትኅን ለማስገኘት ቆርጠው ትግል የጀመሩ ወጣት ኢትዮጵያውያንን ያደራጁት ለራሣቸው ጠባብ አጀንዳ ማሚያና መጠቀሚያ መሣሪያ ለማድረግ ነበር:: ስሌታቸውም ሠርቶላቸዋል:: ይኽንን ድርጅት በአብሪነትና የጠባብ ዓላማው ማስዋቢያና የኢትዮጵያዊነት ጭምብል አድርጎ በመጠቀምና ቆይቶም "የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር -ኢሕአዴግ" የሚል ስያሜ ግንባሩ ላይ ለጥፈው ከትግራይ ደቡብ ወዳለው የአገሪቱ ክፍል ለመገስገስና ደርግን ለማስወገድ የረዳ "ትብብር" ማግኘት አስችሏቸዋል:: የድርጅቱ (ኢሕዴን) አባላት "የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና ለማላቀቅና የአዲስ ሥርዓት ባለቤት ለማድረግ" ነው የምንታገለው ብለው ቢነሱም በተግባር እንደታየው ግን ደርግን በማስወገዱ ረገድ አስተዋፅዖ ከማድረግ ሌላ እንደ-ቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በደርግ አስከፊ ሥርዓት የተማረረው ከትግራይ በስተ-ደቡብ ያለው ሕዝብ ለሕወሓት በሩን ከፍቶ፣ ካለው ቆርሶ

ስንቅ ሰጥቶ፣ መንገድ መርቶ፣ ብዙውም ቤት-ንብረቱን አጥቶ፣ ታግሎና ሞቱንም ሞቶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አጀንዳቸው ያልነበረውን የሕወሓት መሪዎች ለአገራዊ ሥልጣን ማብቃት፣ ብሔራዊ ተቋሞቻችን በሻብያ/ወያኔ ጣምራ ኃይል እንዲመዘበሩ፣ እንዲፈራርሱና እንዲወድሙ፣ ኢትዮጵያም ባሕር-በር አልባ ዝግ አገር እንድትሆን ማድረግን፣ ወዘተ.. ነው ያተረፉት።

ታዲያ "ሲሰማ የሞተን እያየ ቅበረው" እንዲሉ ለዚያ ወሳኝ ሚናውና አገልግሎት ድርጅቱ የተከፈለው ውለታ፣ እንደ ተራ ተከታይ፣ ትዕዛዝ-ፈጻሚና አልፎም ኅብረ-ብሔረሰብ (አገር-አቀፍ) ሆኖ በኢትዮጵያ ስም ያለውን አደረጃጀት እንደ-ያዘ በጉያቸው አቅፈው መቀጠል እነሱ ካላቸው የፖለቲካ ፍልሥፍናና እምነት፣ በዚያም መሠረት በአገሪቱ ላይ ለመዘርጋት ከወጡት የጎሣኝነት ፖለቲካ ጋር አብሮ የማይሄድና ደንቃራ ሆኖ በመገኘቱ፣ እንደገና መጥነው ያዘጋጁለትን "የክልል" ጥብቆ አጥልቆ "አማራ" ለተባለው የኅብረተሰብ ክፍልም አዲስ "ታሪኩ" ተጽፎለት "ብአዴን" በሚል መጠሪያ ተጠምቆ "የአማራ" "ተወካይ" አድርገው ኢትዮጵያዊ ድርሻውን ወስነውለታል።

ትላንት እነ-ኢሕአፓን "ከቦታችን ልቀቁና 'ወደ-አገራችሁ' ሄዳችሁ ታገሉ" ያሉ የሕወሓት ምላጭ መሪዎች እንደ-እነሱ የተወላገደ ጠባብ የጎጠኛ/ጎሠኛ እምነት "የነሱ ወዳልሆነው" የአገሪቱ ክፍል ከመሸጋገር አልፈው አገራዊ ሥልጣን የያዙት የእነሱን አጀንዳ ማሟያ የሚሆን አብሮ-ነጓጂ "የዋህ" ኃይል ከጎናቸው/ከፊታቸው ማሰለፍ በመቻላቸው ነው። ይኸንን እነዚኽ ቡድኖች ጠንቅቀው ያውቃሉ። እነሱስ "የቆምነው ለትግራይ ብቻ ነው" ብለው ቢነሱም፣ ጥያቄአቸው ሲመነዘር ቢበዛ "እኛ የበላይ እንሁን" የሚል ሆኖ ሊገኝ ከመቻሉ ውጭ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ያሉበት ጊዜ ከቶ አልነበረም። በድርጅቱ የተወሰኑ መሪዎች ዘንድ ድብቅ ፀረ-ኢትዮጵያ ዓላማ ቢቀነቀንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች በሕወሓት ሥር የተሰለፈው ወገን አስተሣሰብና ምኞት የደርግን የአፈና አገዛዝ ከማስወገድ ውጭ የአገሩን አንድነት ጥያቄ ውስጥ እንዳላስገባ ጥርጥር አይኖረኝም።

ስለዚኽ ከእነዚኽ ፀረ-አንድነት ቡድኖች ጋር አዲስ "ትብብር" ለመፍጠር የሚደክሙ ወገኖች ጥረታቸው ሕወሓት/ወያነን "ተሸክሞ" ተከዜን ያሻገረውን የኢሕዴንን ስህተት በጣም በባሰ መልኩ መድገም ይሆንባቸዋል። "የባሰ" ስህተት የሚሆነውም እነዚኽኞቹ እንታገልለታለን ብለው ያነገቡት ግብ አገራዊ ሥልጣን ለመያዝ ሣይሆን አገር-ገነጣጣይና አፍራሽ በመሆኑ ነው። ጉዳዩን ይበልጥ ትርጉም-የለሽ የሚያደርገው ደግሞ ከነዚኽ ታጣቂ ኃይሎች ጋር "ትብብር" ለመፍጠር ደፋ-ቀና የሚሉት ወገኖች ባዶ-እጃቸውን መሆናቸውና ሌላው ቢቀር በጊዜው በደንብ የታጠቀ ቢሆንም አንፃራዊ ጥንካሬ ከነበረው ከሕወሓት ከተጠጋው ከ "ኢሕዴን" ትምሕርት ያልቀሰመ አካሄድን መምረጣቸው ነው። እንደሚታወቀው ያ ድርጅት ("ኢሕዴን") እንኳን የአሪቱን የራሱንም ድርጅታዊ ነፃነት ማስከበር እንዳልቻለ ግልጥ ነው።

ሁለተኛ ያለው ዓለም-አቀፍ፣ አካባቢያዊና የአገር-ውስጥ አጠቃላይ ሁኔታዎች በጨቋኝ ሥርዓቶች ሥር የሚገኙ ሕዝቦች አምባ-ገነኖችን አሽቀንጥሮ ለመጣል የተነሣሡበት ጊዜ ነው። በተለይም በአገራችን ሕዝባችንን ጨርሶ መሸከም ያልቻለው፣ በእጅጉ እያንገፈገፈውና እያማረረ ያለውና እየከፋ የሄደው የኑሮ ውድነት ከአጠቃላይ የፖለቲካ ጭቆናው ጋር ተደማምሮ የተፈጠረው ውጥረት፣ ኢትዮጵያውያን በሰሜን-አፍሪቃና በመኻከለኛው-ምሥራቅ የተደረገውና የሚደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በአገራችንም እውን እንዲሆን እንደሚመኙ የማይታበል ሃቅ ነው። በጉዳዩም በርካታ ኢትዮጵያውያን አበክረው እየመከሩበትና ትኩረት የሰጡበት ወቅት ላይ ነው የምንገኘው። ታዲያ ይኸንን የውጥረት ሁኔታና ሕዝብ ለለውጥ ያለውን የጋለ እምቅ ፍላጎት በከፍተኛ ጉጉት የሚመለከቱትና ልዩ ትኩረት አድርገው ሥራየ ብለው የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሣይሆኑ በአንድ በኩል እንደ ሸዓብያ ዓይነት የኢትዮጵያን በጎ የማይመኙና በሌላ በኩል ደግሞ ትግላቸው ከመሬት መነሣት አቅቶት የሚውተረተሩ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-አንድነት ኃይሎች ጭምር ናቸው። አሁን በአለው የአገሪቱ ሁኔታ ይኽ ውጥረት ሊወልድ የሚችለው የሕዝብ መነሣሣት ደግሞ ከማንም ይበልጥ ጠቀሜታ የሚኖረው ለእነዚኽ ቡድኖች እንደሆነ እነሱ አላጡትም። የሩጫው አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው።

ይኽ ሁኔታ ደግሞ በሌጣው የሚታይ ሣይሆን በአንድ በኩልና በዋናነት የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሉ አንፃራዊ የሆነ አሣፋሪ መዳከም ላይ በአለበት፣ ያልተሰባሰበና ስብጥርጥሩ በወጣበት ወቅት ላይ የሚገኝና፣ በአገሪቱም ላይ ዕድሜ ለነ-አቶ መለስ ብሔራዊ አማራጭ ሊሆን የሚችል ሁነኛ አገር-አቀፍ ድርጅትም ሆነ ተቋም በሌለበት፣ በአጠቃላይ አገራችን **ለአደገኛ ክፍተት የተጋለጠችበት ወቅት** ከመሆኑ አንፃር ሊማዘን ይገባል። ይኽ ያፈጠጠ አደጋም ነው ብዙውን አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገን፣ በተለይም የፖለቲካውን አካሄድና ይዞታ በጥሞና የሚመለከቱና የኃይል አሠላለፉን በጥንቃቄ የተገነዘቡ ወገኖች አሁን የሚደረገውን "ትብብርም" ሆነ ሌሎች ተመሣሣይ አዝማሚያዎችና ሂደቶች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጉ አስፈላጊ ነው የሚሉት፣ እየተደረገ ያለውንም መሯሯጥ ትርጉም ያጡለትና አልፎም አምርረው የሚቃወሙት።

**ይቀጥላል.....**